# የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ

ስለ ሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ በሂሳብ ወይም በኦዲት ሙያ ስለመሰማራት እና ስለሙያ ማኅበራት የወጣ ረቂቅ መመሪያ ቁጥር 1/2013

# ለአስተያየት የቀረበ

ጥር 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

DRAFT

**የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 53(2) እና በቦርዱ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 አንቀጽ 32 መሠረት ይህንን ረቂቅ መመሪያ አውጥቷል፡፡**

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ስለ ሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ በሂሳብ ወይም በኦዲት ሙያ ስለመሰማራት እና ስለሙያ ማኅበራት የወጣ ረቂቅ መመሪያ ቁጥር 1/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. **"ቦርድ"** ማለት የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ነው፤

፪. **"አዋጅ"** ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ነው፤

፫. **"ደንብ"** ማለት የኢትዮጵያ የሂሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 ነው፤

፬. **"የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ"** ማለት የተመሰከረላቸው የሂሣብ ባለሙያዎችና ኦዲተሮች የሚመሩበት ቦርዱ የሚያወጣው ወይም ዓለም አቀፍ የሂሳብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል የሚያወጣውና ቦርዱ የተቀበለው የሥነ-ምግባር ደንብ ነው፡፡

፭. **"የሠራተኞች ብዛት"** ማለት ሪፖርት አቅራቢው አካል በሂሣብ ዓመቱ በእያንዳንዱ ወር በሥራ ውል ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሆነው ወሩን ሙሉ ባይሰሩም

ጠቅላላ ድምር በሂሣብ ዓመቱ ላሉት ወራት ቁጥር ሲካፈል የሚገኘው አማካይ የሠራተኞች ብዛት ነው፡፡

፮. **“ጠቅላላ ሀብት”** ማለት በሪፖርት አቅራቢው አካል የሀብትና ዕዳ መግለጫ ላይ የሰፈረው ጠቅላላ የሀብት መጠን ነው፡፡

፯. **“አባል”** ማለት ቦርዱ አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና በሰጠው የሂሳብ ሙያ ማኅበር የተቀመጡትን ሁሉንም መስፈርቶች አሟልቶ የማኅበሩ አባል የሆነ ግለሰብ ነው፡፡

፰. **“በቦርዱ ተቀባይነት ያለው አሰሪ”** ማለት በቦርዱ የተመዘገበ ሪፖርት አቅራቢ አካል፣ የሂሳብ ወይም የኦዲት ድርጅት እና የፌደራል ወይም የክልል የመንግስት መስሪያ ቤት ነው፡፡

፱. **“ከውጭ ኦዲተር የተገኘ የኦዲት የስራ ልምድ”** ማለት በፌደራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት፣ በኦዲት ስራ አገልግሎት ድርጅት ወይም ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው የኦዲት ድርጅት ውስጥ የኦዲትና ማረጋገጥ የስራ ልምድ ያለው፤ እንዲሁም አግባብ ባለው የኦዲት አፈጻጸም እና የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ስርዓት ተቆጣጣሪ መንግስታዊ ተቋም የተገኘ የስራ ልምድ ነው፡፡

፲. **“አገልግሎት ማስቀጠል"** ማለት አንድ የተመሰከረለት የሂሳብ ወይም የኦዲት ባለሙያ በፅኑ ሕመም፣ በሞት፣ ችሎታ በማጣት ወይም ግዴታውን እንዳይፈፅም የሚከለክል ያልታሰበና ድንገት ደራሽ ሁኔታ ሲያጋጥም የጀመረውን አገልግሎት ከቦርዱ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ባለሙያ ለማስቀጠል የሚያስችል ሥርዓት ነው፡፡

፲፩. **“የምዝገባ የምስክር ወረቀት”** ማለት በግል ወይም በሽርክና የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት ለሚፈልግ ሰው በቦርዱ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

፲፪. በአዋጁ አንቀጽ ፪ እና በደንቡ አንቀጽ ፪ ሥር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

፩. ይህ መመሪያ በሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ በተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ በተመሰከረለት ኦዲተር፣ በፐብሊክ ኦዲተር፣ በድርጅቶች እና በሂሳብ ሙያ ማህበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፪. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የምስክር ወረቀት የወሰዱ የተፈቀደላቸው የሂሳብ ባለሙያዎች እና የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርትና ምዝገባ</u>

፬. <u>ሪፖርት አቅራቢ አካላት</u>

በአዋጁ አንቀጽ ፪(፲፯) እና አንቀጽ ፬(፪)(መ) መሠረት የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት እና አነስተኛ ወይም መካከለኛ ድርጅቶች ከዚህ በታች ባሉ አንቀጾች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ናቸው፡፡

፭. <u>የህዝብ ጥቅም ያለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት መለያ መስፈርት</u>

፩. ድርጅቱ ከሚሰጠው የአገልግሎት አይነት ወይም ባህሪ አኳያ፡-

ሀ) የሚያወጡትን የግዴታ የምስክር ወረቀት (Debit or Equity) ቁጥጥር በሚደረግበት ስርዓት ውስጥ ለግብይት ያዋለ ወይም ለማዋል በዝግጅት ላይ ያለ ማንኛውም ኩባንያ፤

ለ) ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች እና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት፤

ሐ) በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ቊጥጥር ስር ያለ የልማት ድርጅት፤

መ) የአክሲዮን ማሕበር (ኩባንያዎች)፤

ሠ) በሚመለከተው የመንግሥት አካል ቁጥጥር የሚደረግበት የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ የሚያስተዳድር እና ተመሳሳይ ተግባር የሚፈጽም ተቋም፤

ረ) የሕብረት ስራ ዩኒየኖች፤

ሰ) ቁጥጥር የሚደረግባቸው የሸማቾች ማሕበራት፤

ሸ) በሚመለከተው አካል ቁጥጥር የሚደረግባቸው የሲቪል ማህበረሰብ እና የበጎ አድራጎት ድርጅት፤

ቀ) የኢትዮጵያ የምርት ገበያ አባላት፤

የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው አካላት ናቸው፡፡

፪. ከድርጅቱ የሀብት መጠንና የሰራተኞች ብዛት አኳያ፡-

ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ያሟላ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል ነው፡፡

ሀ) ዓመታዊ ሽያጩ/ገቢው ብር ፫፻ ሚልዮን (ሦስት መቶ ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

ለ) ጠቅላላ ሀብቱ ወይም ንብረቱ ብር ፪፻ ሚልዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

ሐ) ጠቅላላ ዕዳው ብር ፪፻ ሚልዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) እና ከዚያ በላይ የሆነ፡፡

መ) የሰራተኞቹ ብዛት ፪፻ መቶ (ሁለት መቶ) እና ከዚያ በላይ የሆነ፤

፫. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና ለዚህ መመሪያ አንቀጽ ፮ አፈፃፀም ሲባል የሪፖርት አቅራቢው አካል የሂሳብ ዓመት ፲፪ (አስራ ሁለት) ወራት በማይሞላበት ጊዜ ከፍተኛው የገቢ መጠን ዐሃዞች ተመጣጥኖ ይሰላል፡፡

## ፮. <u>የአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች መለያ መስፈርት</u>

፩. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ያሟላ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅት ነው።

ሀ) ዓመታዊ ሽያጩ/ገቢው ከብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን ብር) እስከ ብር ፫፻ ሚሊዮን (ሦስት መቶ ሚሊዮን ብር) የሆነ፤

ለ) ጠቅላላ ሀብቱ ወይም ንብረቱ ከብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን ብር) እስከ ብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) የሆነ፤

ሐ) ጠቅላላ ዕዳው ከብር ፳ ሚሊዮን (ሃያ ሚሊዮን ብር) እስከ ብር ፪፻ ሚሊዮን (ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) የሆነ፤

መ) የሰራተኞቹ ብዛት ከ፳ (ሃያ) እስከ ፪፻ (ሁለት መቶ) የሆነ፤

፪. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ሥር የተዘረዘሩትን የማያሟላ ማንኛውም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅት ነው።

፫. ዕዳውን ወይም የአክሲዮን ድርሻውን ቁጥጥር በሚደረግበት የካፒታል ገበያ ላይ ያላዋለ ወይም ለማዋል በዝግጅት ላይ ያልሆነ፤

፬. የብዙ ሰዎች ሃብት ወይም ንብረት የማስተዳደር ኃላፊነት የሌለበት ከሆነ፤

## ፬. <u>የጥቃቅን ድርጅቶች መለያ መስፈርት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፫ እና ፬ ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የማያሟላ የሽርክና ማኅበር ወይም የግል የንግድ ድርጅት እንደ ጥቃቅን ድርጅት ይቆጠራል።

## ፭. <u>የሪፖርት አቅራቢ አካል ግዴታዎች</u>

፩. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ተገቢውን ክፍያ በመክፈል ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት በየዓመቱ ኦዲት የተደረገ የተሟላ የሂሳብ ሪፖርት መግለጫዎች ማቅረብ አለበት።

ሀ) የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል ከሆነ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤

ለ) አነስተኛ ወይም መካከለኛ ድርጅት ከሆነ ለአነስተኛ ወይም መካከለኛ ድርጅት በወጣው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች፤

ሐ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ከሆነ በዓለም አቀፍ የፐብሊክ ሴክተር የሂሳብ አያያዝ ደረጃዎች፡፡

፪. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሚያቀርበው ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫ በዚህ አንቀፅ በተደነገገው የፋይናንስ ደረጃ እና ቦርዱ በተቀበላቸው የኦዲት ደረጃዎች መሰረት ተዘጋጅቶ በቅድሚያ ለቦርዱ መቅረብ ያለበት ሲሆን በሌሎች ህጎች ስልጣን ለተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት የሚቀርበው ሪፖርትም ለቦርዱ የቀረበው ኦርጂናል ቅጂ መሆን አለበት፡፡

፫. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሪፖርት አቅራቢ አካላት ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫቸውን ለቦርዱ ሲያቀርቡ እንደአግባብነቱ በተመሰከረለት ኦዲተር ወይም በፐብሊክ ኦዲተር የማስመርመር ግዴታ አለባቸው፡፡

፬.በዚህ አንቀጽ የተጠቀሱ ሪፖርት አቅራቢ አካላት ኦዲት የተደረገ የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን የድርጅቱ የሂሳብ ዓመት በተጠናቀቀ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ቦርዱ በሚወስነው የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴ በመጠቀም ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ያላቀረበ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ፭፻ (አምስት መቶ) ብር እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ስራ አስኪያጅ ፫፻ (ሦስት መቶ) ብር የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ለ፫ (ሶስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፮. ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በቦርዱ ያልተመዘገበ ሪፖርት አቅራቢ አካል ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ ካልተመዘገበ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ፭፻ (አምስት መቶ) ብር እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ስራ አስኪያጅ ፫፻ (ሦስት መቶ) ብር የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው

ለ፫ (ሦስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፯. ይህ መመሪያ ከወጣ በኃላ የተመሰረተ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል ከተመሰረተበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሶስት ወራት ውስጥ ካልተመዘገበ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሪፖርት አቅራቢው አካል ፭፻ (አምስት መቶ) ብር እና የሪፖርት አቅራቢው አካል ስራ አስኪያጅ ፫፻ (ሶስት መቶ) ብር የገንዘብ ቅጣት ይከፍላል፡፡ ሆኖም ይህ የገንዘብ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው ለ፫ (ሦስት) ወር ብቻ ሲሆን ሦስት ወር ካለፈ በአዋጁ አንቀጽ ፵፬ ድንጋጌ መሰረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፡፡

8. ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ አካል የሂሳብ እና የኦዲት ስራ ሲያሰራ ከሚሰራለት ባለሙያ ጋር ሕጋዊ ውል መዋዋል አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ የሚያቀርበው የሂሳብ መግለጫ እና የኦዲት ሪፖርት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ስለተመሰከረለት ኦዲተር፣ፐብሊክ ኦዲተር እና ድርጅቶች</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>የምዝገባ የምሥክር ወረቀት አሰጣጥ</u>

### ፱. <u>እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብ እና በግል ወይም በሽርክና የሂሳብ ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መሰፈርቶች</u>

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ እና የሂሳብ ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና የክፍያ ደረሰኝ በማያያዝ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

፪. እንደተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ለመመዝገብና በግል ወይም በሽርክና የሂሳብ ስራ ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በደንቡ አንቀጽ ፲፯(፫) እና ፳ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ፡-

ሀ) ቦርዱ በሚያስተዳድረው እና/ወይም ዕውቅና በሰጠው የሂሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ፤

ለ) የሂሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከመሆኑ በፊት ወይም ከሆነ በኋላ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት ካመለከተበት ቀን በፊት ባሉት አምስት (፭) ዓመታት ውስጥ ለሶስት (፫) ዓመታት በቦርዱ ተቀባይነት ያለው አሠሪ ዘንድ በሂሣብ ሙያ ወይም በኦዲተርነት የሥራ ልምድ ያለው፤

ሐ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ለ) እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ አገር የተገኘ የስራ ልምድ ከሆነ በቦርዱ ተቀባይነት ባለው አሰሪ ዘንድ ቢያንስ ለአንድ (፩) አመት በሂሳብ ሙያ ወይም በኦዲተርነት የሰራ፤

መ) የሙያ ማህበር አባል ከሆነ አንድ አመት ያለፈው አመልካች ከሆነ በቦርዱ ቀጣይነት ያለው የሙያ ማጎልበቻ ፖሊሲ መሠረት ለእያንዳንዱ አመት ቢያንስ አርባ (፵) ሰዓት/ዩኒት ያለው ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ የወሰደ/ያለው ከዚህ ውስጥ ሃያ (፳) ሰዓት/ዩኒት በማስረጃ አስደግፎ በቦርዱ የተዘጋጀውን የማረጋገጫ ቅጽ ሞልቶ ያቀረበ፤

ሠ) ከሰራበት ድርጅት የቅርብ ኃላፊ እና የድርጅቱን ሂሳብ ኦዲት ካደረገ የውጭ ኦዲተር የተሰጠ አስተያየት ያቀረበ፤ አመልካቹ በኦዲተርነት ሲሰራ የነበረ ከሆነ ከሰራባቸው ድርጅቶች የቅርብ ኃላፊ የተሰጠ ሁለት (፪) አስተያየት ማቅረብ አለበት።

፫. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱን ቦርዱ ሲያረጋግጥ፡-

ሀ) ባለፉት አምስት (፭) ዓመታት በማንኛውም ተቋም በከባድ አስተዳደራዊ እርምጃ/በዲሲፕሊን ክስ ያልተቀጣ ለመሆኑ ማረጋገጫ እንዲሰጥ፤

ለ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው እና በእምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተሳታፊ ሆኖ በማንኛውም ሀገር ጥፋተኛ ያልተባለ መሆኑን የማረጋገጫ ቅጽ ሞልቶ እንዲያቀርብ፤

ሐ) የቦርዱን የሙያ ሥነ-ምግባርና የዲሲፕሊን ሥነ ሥርዓት ደንብ ለማክበር ማረጋገጫ እንዲሰጥ፤

መ) በግል የሂሳብ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ በሞት ወይም በችሎታ ማጣት ምክንያት አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ የማድረጊያ ስምምነት ያለው መሆኑን ማረጋገጫ እንዲያቀርብ፤

ሠ) መጨረሻ ከሰራበት ተቋም የሥራ መልቀቂያ እንዲያቀርብ፤

ረ) በቦርዱ ተቀባይነት ያለው የድርጅት ስም እንዲያቀርብ፤

ሰ) አመልካቹ ለስራ የሚጠቀምበት ቢሮ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ኤጀንሲ የተረጋገጠና የተመዘገበ የኪራይ ውል ወይም የመንግስት ቤት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር የተደረገ የኪራይ ውል እንዲያቀርብ፤

ሸ) የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ እና

ቀ) በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው የፓስፖርት መጠን ያለው አንድ ፎቶግራፍ እንዲያቀርብ፤

በማድረግ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

፬. ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል በግልም ሆነ በመንግስት የትምህርት ተቋማት በማስተማር የተገኘ የስራ ልምድ እንደ የሂሳብ ወይም የኦዲት ስራ ልምድ አይያዝም።

፭. የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የ፭፻ ሺ (አምስት መቶ ሺ) ብር የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና፣ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ በሽርክና የተቋቋመ ሲሆን መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፪ (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።

፮. ከቦርዱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የወሰደ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሰረት ካልፈጸመ የሂሳብ ስራ አገልግሎት ለመስጠት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ምዝገባው ይሰረዛል።

## ፲. እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ እና በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ሙያ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶች

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ እና የኦዲት ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና የክፍያ ደረሰኝ በማያያዝ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

፪. እንደተመሰከረለት ኦዲተር ለመመዝገብ እና በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ስራ ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በደንቡ አንቀጽ ፲፰(፫) እና ፳ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፡-

ሀ) ቦርዱ አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና በሰጠው የሂሣብ ሙያ ማኅበር ውስጥ ከሶስት (፫) ላላነሱ ዓመታት ሳያቋርጥ አባል የሆነና ግዴታውን የተወጣ፤

ለ) አባል ከሆነበት የሙያ ማኅበር ወይም ኢንስትቲዩት የፀና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት (Practicing Certificate) ያቀረበ፤

ሐ) የሂሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከሆነ በኋላ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ለማግኘት ካመለከተበት ቀን በፊት ባሉት አምስት (፭) ዓመታት ውስጥ በውጭ የኦዲት ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለሶስት (፫) ዓመታት በኦዲተርነት የሥራ ልምድ ያለው እና ከዚህ ውስጥ ለሁለት (፪) አመታት በኦዲት ማናጀርነት የሥራ ልምድ ያለው፤

መ) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ሐ) እንደተጠበቀ ሆኖ በውጭ አገር የተገኘ የስራ ልምድ ከሆነ በቦርዱ በተመዘገበ የኦዲት ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለአንድ (፩) አመት በኦዲተርነት የሰራ፤

ሠ) አባል ከሆነ በኋላ በቦርዱ ቀጣይነት ያለው የሙያ ማጎልበቻ ፖሊሲ መሠረት ለእያንዳንዱ አመት ቢያንስ አርባ (፵) ሰዓት/ዩኒት ያለው ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ የወሰደ/ያለው ከዚህ ውስጥ ሃያ (፳) ሰዓት/ዩኒት የኦዲትና ማረጋገጥ ትምህርት የወሰደና

በትጋት ስለመከታተሉ በማስረጃ አስደግፎ በቦርዱ የተዘጋጀውን የማረጋገጫ ቅጽ ሞልቶ የሚያቀርብ፤

ረ) መጨረሻ ከሰራበት ድርጅት የቅርብ ኃላፊ እና ባለሙያው የተሳተፈበት አሰሪው ድርጅት ኦዲት ካደረገው ሪፖርት አቅራቢ አካል የተሰጠ አስተያየት ያቀረበ፤

፫. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ ፫ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱን ቦርዱ ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፬. የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የብር ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና፣ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ በሽርክና የተቋቋመ ሲሆን መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፪ (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

፭. ከቦርዱ የምስክር ወረቀት የወሰደ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት ካልፈጸመ የኦዲት ስራ አገልግሎት ለመስጠት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ምዝገባው ይሰረዛል፡፡

## ፲፩. <u>እንደ ፐብሊክ ኦዲተር ለመመዝገብ እና በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ስራ ለመስራት የሚያስፈልጉ መሥፈርቶች</u>

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላና የኦዲት ስራ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ የተመሰከረለት ኦዲተር ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላትና የክፍያ ደረሰኝ በማያያዝ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡

፪. እንደ ፐብሊክ ኦዲተር ለመመዝገብና በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ስራ ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ፡-

ሀ) ከአምስት ላላነሱ ዓመታት ሳያቋርጥ ቦርዱ አክሬዴሽን ወይም ዕውቅና በሠጠው የሂሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነና ግዴታውን የተወጣ፤

ለ) አባል ከሆነበት የሙያ ማኅበር የፀና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት (Practicing Certificate) ያቀረበ፤

ሐ) የተመሰከረለት ኦዲተር የሆነና በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ድርጅት አቋቁሞ ለሶስት ዓመታት የኦዲት ስራ አገልግሎት የሰጠ፤

መ) በቦርዱ ቀጣይነት ያለው የሙያ ማጎልበቻ ፖሊሲ መሠረት ለእያንዳንዱ አመት ቢያንስ አርባ (፵) ሰዓት/ዩኒት ያለው ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ የወሰደ/ያለው ከዚህ ውስጥ ሃያ (፳) ሰዓት/ዩኒት የኦዲትና ማረጋገጥ ትምህርት የወሰደና በትጋት ስለመከታተሉ በማስረጃ አስደግፎ በቦርዱ የተዘጋጀውን የማረጋገጫ ቅጽ ሞልቶ ያቀረበ፤

፫. አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፫) (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) እና (ረ) ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ በቦርዱ ሲያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

፬. የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የብር ፭ ሚሊዮን (አምስት ሚሊዮን ብር) የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና፣ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ በሽርክና የተቋቋመ ሲሆን መመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፪ (ሁለት) ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

፭. ከቦርዱ የምስክር ወረቀት የወሰደ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሰረት ካልፈጸመ እንደፐብሊክ ኦዲተር አገልግሎት ለመስጠት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ ምዝገባው ይሰረዛል፡፡

## ፲፪. የድርጅቶች ትሥሥርና ስም አሠጣጥ

፩. የዓለም ዓቀፍ ኦዲት ትሥሥር ድርጅት አባል የሆነ አንድ የኦዲት ድርጅት የትሥሥር ድርጅቱን ስም ከመጠቀሙ/ከመቀበሉ በፊት ለቦርዱ የግንኙነቱን ዝርዝር ጨምሮ፡-

ሀ) የድርጅቱን የባለቤትነት መዋቅር፤

ለ) የትርፍና/ወጪ ክፍፍሉን ሥርዓት፤

ሐ) የትሥሥር ሥርዓቱ የሚያስከትለውን የጋራ ፖሊሲዎች፣ ሥነ ሥርዓቶች፣ ስምና እስትራቴጂ፤

መ) የባለሙያ አቅርቦቶች የመጋራት ሥርዓቶችን (ካለ)ማሣወቅ ይኖርበታል፡፡

፪. አንድ የኦዲት ድርጅት አባል የሆነበትን የኦዲት ትሥሥር ስም መጠቀም ወይም መቀበል የሚችለው ቦርዱ ዝርዝር የትሥሥር ሥርዓቱን መርምሮ፣ ስያሜውንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን ከተቀበለው ብቻ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የምስክር ወረቀት እድሳት</u>

### ፲፫. <u>የምዝገባ ምሥክር ወረቀት ዕድሳት</u>

፩. በቦርዱ የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡

፪. የተሰጠበት ቀን ግምት ውስጥ ሳይገባ የምዝገባ የምሥክር ወረቀት የሚፀናው በየዓመቱ እስከ ጥር ሰላሳ (፴) ድረስ ነው፡፡

፫. የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ (፩) ወር በፊት የእድሳት ማመልከቻ መቅረብ አለበት፡፡ የአገልግሎት ጊዜው ካበቃ በኋላ የሚቀርብ የምስክር ወረቀት እድሳት ማመልከቻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ መሰረት በቅጣት ይስተናገዳል፡ ፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተገለፀው ቢኖርም በማንኛውም ሁኔታ ሳይታደስ አንድ (፩) ዓመት ያለፈው የምዝገባ ምሥክር ወረቀት ይሰረዛል፡፡

፭. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፬) የተደነገገው ቢኖርም የምስክር ወረቀቱ ያልታደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት (፮) ወር ድረስ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፡፡

፮. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሰረት የቀረበ ማመልከቻ በኮሚቴ ታይቶ ተቀባይነት ካገኘና በኮሚቴው የሚቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በዋና ዳይሬክተሩ ከፀደቀ የማሳደሻውን ክፍያ ከነቅጣቱ በመክፈል የምስክር ወረቀቱ ሊታደስ ይችላል፡፡

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፮) መሰረት የሚቀርብ የእድሳት ማመልከቻን ገምግሞ የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ሶስት አባላት ያሉት ኮሚቴ በቦርዱ ዋና ዳይሬክተር ይዋቀራል፡፡

**፲፩. የምዝገባ የምሥክር ወረቀት ለማሳደስ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

ማንኛውም የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ የሂሳብ ባለሙያ፣ ኦዲተር ፣ ፐብሊክ ኦዲተር ወይም ድርጅት፡-

ሀ) የእድሳት ማመልከቻና የክፍያ ደረሠኝ፤

ለ) ቦርዱ አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ከሰጠው የሂሣብ ሙያ ማኅበር አባል ሆኖ ግዴታውን የተወጣ (Member in good standing) ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤

ሐ) የተመሰከረለት ኦዲተር እና ፐብሊክ ኦዲተር ሲሆን የፀና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት (Practicing Certificate) ፤

መ) በቦርዱ ቀጣይነት ያለው የሙያ ማጎልበቻ ፖሊሲ መሠረት አንድ ዓመት ያላለፈው ቢያንስ አርባ (፵) ሰዓት/ዩኒት ያለው ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ የወሰደ/ያለው ከዚህ ውስጥ ሃያ (፳) ሰዓት/ዩኒት ስለመከታተሉ ማስረጃ፤

ሠ) እንደአግባብነቱ የጸና የሙያ መድን ሽፋን የሚያቀርብ መሆኑን፤

ረ) በግል/በተናጠል የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ በሞት ወይም በችሎታ ማጣት ምክንያት ሥራው እንዳይቋረጥ አገልግሎት ማስቀጠል የሚያስችል ከቦርዱ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ባለሙያ ጋር ውል ያለው መሆኑን፤

ሰ) በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የነበሩትን የደንበኞቹን ዝርዝር፣ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ከደንበኛ የተቀበለውን ክፍያ፣ የደንበኞቹን አድራሻና የተሰማሩበትን የንግድ ወይም የሥራ ዘርፍ፣ ስራው የተጀመረበትና የተጠናቀቀበትን ጊዜ እና ሥራውን ያከናወነው ሽሪክ/ፈራሚ ስም ያካተተ ዓመታዊ የሥራ ሪፖርት፤

ሸ) የሂሳብ ስራ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ከሆነ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ ፣ የኦዲት ድርጅት ሲሆን የድርጅቱ ኦዲት የተደረገ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫ፤

ቀ) የኦዲት ድርጅት ከሆነ በአለም አቀፍ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ደረጃ መሠረት ውጤታማ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት መተግበሩን ማረጋገጫ፤

በ) አመልካቹ ለስራ የሚጠቀምበት ቢሮ የራሱ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም ከሌላ ሰው የተከራየው ከሆነ ጊዜው ያላለፈበት በሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ኤጀንሲ የተረጋገጠና የተመዘገበ የኪራይ ውል ወይም የመንግስት ቤት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር የተደረገ የኪራይ ውል፤ እና

ተ) የፀና ንግድ ፈቃድ

በማቅረብ ማሳደስ ይችላል፡፡

## ፲፭. የማመልከቻ ጊዜው ካለፈ በኋላ ስለሚቀርብ የእድሳት ጥያቄ

በዚህ መመሪያ አንቀፅ ፲፫ ንዑስ አንቀፅ (፫) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የእድሳት ማመልከቻ ያላቀረበ ፦

ሀ) የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፩፻ (አንድ መቶ) ብር

ለ) በሽርክና የሂሳብ ሙያ አገልግሎት ለሚሰጥ ድርጅት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፪፻ (ሁለት መቶ) ብር

ሐ) የተመሰከረለት ኦዲተር ለሆነ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፪፻ (ሁለት መቶ) ብር

መ) በሽርክና የኦዲት ሙያ አገልግሎት ለሚሰጥ ድርጅት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፫፻ (ሶስት መቶ) ብር

ሠ) የፐብሊክ ኦዲተር የሙያ ፈቃድ ምስክር ወረቀት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፫፻ (ሶስት መቶ) ብር

ረ) በሽርክና በፐብሊክ ኦዲተርነት አገልግሎት ለሚሰጥ ድርጅት ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ፬፻ (አራት መቶ) ብር

ቅጣት በመክፈል የምስክር ወረቀቱን ሊያሳድስ ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>የተከለከሉ ተግባራት፣ እገዳን ስለማንሳት እና መልሶ ስለመመዝገብ</u>

### ፲፮. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

በአዋጁና በደንቡ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ፐብሊክ ኦዲተር እና ድርጅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባራት መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

ሀ) የቦርዱ ሠራተኛ ሥራውን በሚመለከት ለሚያቀርበው ጥያቄ አለመተባበር፤

ለ) ስለሙያው በቂ እውቀት የሌላቸውን ሰራተኞች ቀጥሮ ማሰራት፤

ሐ) የደንበኞችን መረጃ በአግባቡ አደራጅቶ አለመያዝ፤

መ) በስሩ ቀጥሮ የሚያሰራቸውን ሰራተኞች መረጃ በአግባቡ አለመያዝና ለቦርዱ አለማሳወቅ፤

ሠ) የአድራሻ፣ የድርጅት ስም እና ማናቸውም መረጃዎች ላይ ለውጦች ሲኖሩ በአስራ አራት (፲፬) ቀናት ውስጥ አለማሳወቅ፤

ረ) የሙያ ሥነ-ምግባርና የአሰራር ደንብ እና የሙያ አፈፃፀም ደረጃዎች ጥሰት መፈፀም፤

ሰ) በማስመሰል ወይም በማጭበርበር መመዝገብ ፣ ለመመዝገብ መሞከር ፣ ማሳደስ ወይም ለማሳደስ መሞከር፤

ሸ) የቴክኒክ ማጣቀሻዎችን የሚጥስ ድርጊት መፈጸም፤

ቀ) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣንና ለሌላ አግባብ ላለው የመንግስት አካል ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ መስጠት፤

በ) የቦርዱ ሠራተኛ ሥራውን በሚመለከት ለሚያቀርበው ጥያቄ መሰናክል መፍጠር ወይም ሀሰተኛ መረጃ መስጠት፤ ወደ ላይ ቢሄድ

ተ) በታገደ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት፤

ቸ) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይዞ የንግድ ስራ ፈቃድ ሳይኖረው የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት፤

ኀ) በግልም ሆነ በሽርክና የሂሳብ ወይም የኦዲት ስራ ለመስራት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከወሰደ/ዱ በኋላ የምስክር ወረቀቱን ተመላሽ ሳያደርግ/ጉ ተቀጥሮ መስራት፤

ነ) የምስክር ወረቀቱ ከሚፈቅደው የሙያ አገልግሎት ውጭ መስራት፤

ኘ) የሂሳብ ወይም የኦዲት ሥራ አገልግሎት ለመስጠት ከደንበኛው ጋር የተደረገ የጽሁፍ ውል ሳይኖረው አገልግሎት መስጠት፤

አ) እራሱ ባላዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ላይ ማህተም አድርጎ መገኘት፤

ከ) የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሌላ ሰው እንዲገለገልበት አሳልፎ መስጠት ወይም የሙያ ሥራውን በውክልና ማሰራት፤

□) ባልታደሰ የምዝገባ የምስክር ወረቀት መስራት

ወ) የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወስዶ የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና፣ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ በሽርክና የተቋቋመ ሲሆን የመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ሳያቀረብ የሂሳብ ወይም የኦዲት ስራ መስራት እና

ዐ) በሂሳብ ወይም በኦዲት ድርጅት ውስጥ ሽሪክ የሆነ ባለሙያ በግሉ የሂሳብም ሆነ የኦዲት አገልግሎት መስጠት።

## ፲፯. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩. የቦርዱ ክስ ሰሚዎች አዋጁ፣ ደንቡ እና ይህ መመሪያ በተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ በተመሰከረለት ኦዲተር፣ በፐብሊክ ኦዲተር ወይም ድርጅት መጣሱን ሲያረጋግጡ በአዋጁና በደንቡ የተቀመጡትን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስናሉ፡፡

፪. የምሥክር ወረቀቱ የታገደ ወይም የተሰረዘ ማንኛውም ድርጅት ወይም ግለሰብ ቦርዱ የዕገዳውን ወይም የስረዛውን ውሳኔ ባሳወቀበት ደብዳቤ ላይ ከተጠቀሰው የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አስር (፲) የሥራ ቀናት ውስጥ ከቦርዱ የተሰጠውን ዋናውን የምሥክር ወረቀት ለቦርዱ መመለስ አለበት፡፡

፫. በዚህ መመሪያ መሠረት ቦርዱ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ የንግድ ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር ኃላፊነት ለተሰጠው እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

፬. በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ መሠረት የተወሰነ ማንኛውም የቅጣት ውሳኔ በባለሙያው ወይም ድርጅቱ የግል ማኅደር ውስጥ እንዲመዘገብ/እንዲያያዝ ይደረጋል፡፡

፲፰. <u>ስለ ምስክር ወረቀት እገዳ</u>

፩. የቦርዱ ክስ ሰሚዎች የሚወስኑት የምዝገባ የምስክር ወረቀት እገዳ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ከመቶ ሰማንያ (፻፹) ቀናት ሊበልጥ አይችልም፡፡

፪. በአዋጁ፣ በደንቡና በዚህ መመሪያ መሠረት የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በክስ ሰሚዎች የታገደ የተመሰከረለት የሂሳብ ባለሙያ፣ የተመሰከረለት ኦዲተር፣ ፐብሊክ ኦዲተር እና ድርጅት የእገዳ ጊዜው ሲያበቃ እገዳው እንዲነሳለት በአስር (፲) የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከት አለበት፡፡

፫. እገዳውን ያስተላለፉት ክስ ሰሚዎች ወይም እነርሱ በማይኖርበት ጊዜ በዋና ዳይሬክተር የሚሰየሙት ማመልከቻውን ተቀብለው ከመረመሩ በኋላ ለእገዳው ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በአግባቡ መስተካከላቸውን ካመኑ እገዳውን ሊያነሱ ይችላሉ፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እገዳው እንዲነሳለት ካላመለከተ ወይም ለእገዳው ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች መስተካከላቸው ካልታመነ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

፭. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እገዳው እንዲነሳለት ያላመለከተው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በመግለጽ በስድስት (፮) ወር ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አፈጻጸሙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) መሰረት ይሆናል፡፡

## ፲፱. መልሶ ስለመመዝገብ

፩. በማንኛውም ምክንያት ከመዝገብ የተሰረዘ ባለሙያ ወይም ድርጅት በድጋሚ ለመመዝገብ በአዋጁ፣ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ በተደነገጉት መሰረት እንደ አዲስ ማመልከት አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃዱ ወይም ምዝገባው የተሰረዘው በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፲፮(፪) በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ፈቃዱን/የምስክር ወረቀቱን ባለማሳደሱ ከሆነ ፈቃዱ/የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ እንደ አዲስ ማመልከት አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## የሂሳብ ሙያ ማኅበራት አክሬዲቴሽን እና ዕውቅና

## ፳. በሀገር ውስጥ ለተቋቋመ የሙያ ማኅበር አክሬዲቴሽን ስለመስጠት

፩. ቦርዱ ያስቀመጣቸውን መሥፈርቶች ላሟላ ሀገር በቀል ማኅበር እና ቅርንጫፉ እንደ ሒሣብ ሙያ ማኅበር የአክሬዲቴሽን ምስክር ወረቀት ይሠጣል፡፡

፪. የሙያ ማኅበሩ እና ቅርንጫፉ አክሬዲቴሽን ለማግኘት በአዋጁ አንቀጽ ፳፮ እና ፳፯ ከተደነገገው በተጨማሪ ቦርዱን በሚያሳምን ሁኔታ፡-

ሀ) የዓለም አቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን አባል የሆነ ወይም ለመሆን የሚያስችለውን ፕሮግራም ቀርፆ የሚንቀሳቀስ ስለመሆኑ፤

ለ) ለቅርንጫፉ አክሬዲቴሽን እንዲሰጥ ለቦርዱ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት የማኅበሩ ምክር ቤት ቅርንጫፉን ለመክፈት የወሰነ ስለመሆኑ፤

ሐ) በፋይናንስም ሆነ በአሠራሩ ረገድ ፀንቶ በሥራ ላይ የቆየ ወይም ለመቆየት የሚያስችለው ፕሮግራም ያለው እና ለወደፊትም እንደሚቀጥል ሊገመት የሚችል ስለመሆኑ

መ) ቢሮ ያለው ስለመሆኑ፤

ሠ) የማቋቋሚያ ሕግ (Constitution) ሰነድ የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

ረ) የመተዳደሪ ደንብ እና የመመስረቻ ቃለ-ጉባዔ/ጽሁፍ የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

ሰ) የቀጣይነት የአጭርና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ ዕቅድ እና የመፈጸም አቅምን የሚያሳይ ሰነድ የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

ሸ) ትርፍና ኪሳራ እንዲሁም ሀብትና እዳ የሚገልጽ ሪፖርት የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

ቀ) የአባላቱን ብዛት በጾታና ሙያቸው ዝርዝር መረጃ የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

በ) በጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ ድርጅታዊ መዋቅር የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤

ተ) የማኔጅመንት ወይም የአመራር ብዛት መረጃ የሚያቀርብ ስለመሆኑ፤ እና

ቸ) በቋሚነት የቀጠራቸው የሰው ሃይል ወይም ባለሙያዎች ብዛት መረጃ የሚያቀርብ ስለመሆኑ

ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

**<u>፳፩. በውጭ አገር ለተቋቋመ የሙያ ማኅበር ዕውቅና ስለመስጠት</u>**

፩. ቦርዱ ያስቀመጣቸውን መሥፈርቶች ላሟላ በውጪ አገር ለተቋቋመ የሙያ ማኅበር እና ቅርንጫፉ እንደ ሂሣብ ሙያ ማኅበር የዕውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

፪. የሙያ ማኅበሩ እና ቅርንጫፉ ዕውቅና ለማግኘት በአዋጁ አንቀጽ ፳፮(፪) እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20(2) (መ እስከ ቸ) ለአገር ውስጥ ከተደነገገው መስፈርት በተጨማሪ ቦርዱን በሚያሳምን ሁኔታ፡-

ሀ) የዓለም ዓቀፍ የሂሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን አባል ስለመሆኑና የአባልነት ግዴታውን ስለማክበሩ፤

ለ) ለቅርንጫፉ እውቅና እንዲሰጥ ለቦርዱ ማመልከቻ ከማቅረቡ በፊት የማኅበሩ ምክር ቤት ቅርንጫፉን ለመክፈት የወሰነ ስለመሆኑ፤

ሐ) በፋይናንስም ሆነ በአሠራሩ ረገድ ፀንቶ በሥራ ላይ የቆየና ለወደፊትም እንደሚቀጥል ሊገመት የሚችል ስለመሆኑ፤

ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

**<u>፳፪. አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩. ቦርዱ እንደሂሣብ ሙያ ማኅበር አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና እንዲሰጠው የሚፈልግ በሀገር ውስጥ ወይም በውጪ ሀገር የተቋቋመ የሙያ ማኅበር እና ቅርንጫፉ ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የምዝገባ ክፍያ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

## ፳፫. <u>አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ይዞ ስለመቀጠል</u>

፩. ማንኛውም የሂሳብ ሙያ ማህበር የተሰጠውን አክሬዲቴሽን ወይም እውቅና ይዞ ለመቀጠል፡-

ሀ) ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ከአገልግሎት ክፍያ ጋር ማቅረብ አለበት፤

ለ) አክሪዲቴሽን ይዞ ለመቀጠል በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፣ እውቅናን ይዞ ለመቀጠል በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡

፪. በቦርዱ የተሠጠን ዕውቅና ወይም አክሬዲቴሽን ይዞ ለመቀጠል የሚቀርብ ማመልከቻ የሙያ ማህበሩ የሂሳብ ዓመቱ ባለቀ በሁለት (፪) ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ዕውቅና ወይም አክሬዲቴሽን ይዞ ለመቀጠል የቀረበን ማመልከቻ ቦርዱ ሳያይ የአገልግሎት ጊዜው ካለፈ ማመልከቻውን አይቶ እስኪወስን ድረስ ዕውቅናው ወይም አክሪዲቴሽኑ የሚቀጥል ሆኖ ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ እውቅናው ወይም አክሪዲቴሽኑ የአገልግሎት ጊዜ ካለቀበት ቀን ጀምሮ እንደሚያገለግል ይቆጠራል፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሰረት ዕውቅናን ወይም አክሬዲቴሽንን ይዞ ለመቀጠል የሚያስችል ፈቃድ ካላገኘ እውቅናው ወይም አክሬዲቴሽኑ ይሰረዛል፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

# <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

## ፳፬. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በቦርዱ የፈቃድ አሰጣጥ የአሰራር ሥርዓት መሰረት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ((የግል) Individual) ብቻ ወስዶ የሂሳብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ ባለሙያ እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (5)፤ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (2)(ረ) እና (3) ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች

በማሟለት ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ6 ወራት ውስጥ ከቦርዱ የምዝገባ ምስክር ወረቀት መውሰድ አለበት፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ያልወሰደ ባለሙያ የሂሳብ ወይም የኦዲት ስራ አገልግሎት ለመስጠት እንዳልፈለገ ተቆጥሮ የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

## ፷፭. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ የውስጥ ደንብ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፷፮. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከሕዳር ---- ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ---- ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም**

**የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ**